# ★ ዴሞክራሲያ ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞክራሲያ ቅጽ 38 ቁጥር 2 ኅዳር 2005 ዓ.ም


## እሾህን ሳያስወግዱ፣ እንደልብ አይራመዱ

በአለፈው ግማሽ ምዕተ-ዓመት በኢትዮጵያ የፖለቲካ መልከዓ-ምድር ውስጥ ሦስት የተለያዩ የመንግሥት ሥርዓቶች እንደተለዋወጡ ሁሉም የሚያወቀው ነው:: የዚህ ክስተት ሂደት ግን ያምስቱን ዓመታት የኢጣሊያ የቅኝ ግዛት ወራርን አይጨምርም:: የኢጣሊያ ወረራ፣ በመነሻውም ይሁን በመድረሻው፣ ባፈጣጠሩም ይሁን በዓላማውና ይዘቱ፣ የተለየ በመሆኑ፣ ከሦስቱ ሥርዓቶች ጋር ለንፅፅር ሊቀርብ የማይገባው መሆኑን ብናስተውልም፣ ከሀገራችን መዋረድና ከሕዝባችን መከራና ስቃይ አኳያ ሲታይ ግን በታሪክ አብሮ የሚታይ ክስተት ከመሆን አያልፍም:: ምክንያቱም በተገዥው ሕዝብ ላይ ከሚደርሰው እመቃና ጭቆና አንጻር ደረጃቸውና መንፈሳቸው የተለያየ ቢሆንም የሚመሳሰሉባቸው በርካታ ነገሮች ሊኖሩ ስለሚችሉ ነው::

**“መልካም ዘመን እስኪመጣ፣ ድርስ የአባቴ አገልጋይ ይግዛኝ ”** የሚለው ይትበኃል፣ ምናልባት ለሥነ-አዕምሮ ማባበያ ሊረዳ ይችል እንደሁ እንጅ፣ ከመሠረታዊ ነፃነትና ከሕዝብ ልዕልና፣ ከሰብዓዊ መብትና ከዴሞክራሲ ሥርዓት አንፃር ሲገመገም፣ የሕዝብን ስቃይና መከራ ሊያቃልለውም ይሁን ሊለውጠው አይችልም:: ያ መሠረታዊ ለውጥ ካልተገኘ ደግሞ የሕዝብ ትግልና አመፅ ይቀጥላል እንጅ ፈፅሞ አይዳፈንም:: የአምባገነን ሥርዓት አራማጆች ግን ይህን የማይታበል ቃል ለማመን ስለማይፈልጉ፣ ወደ ከርሰ-መቃብራቸው እስከ ሚወርዱበት ጊዜ ድረስ ከሥልጣናቸው በፈቃዳቸው አይወርዱም:: ይልቁንም፣ ሕዝብ መጨቆንን ተቀዋሚዎቻቸውን ማጥፋትንና የሀገርን ሀብት እየዘረፉ ማሸሹን በሰፊው ይቀጥሉበታል:: ለዚህም የተፈራረቁት የአምባገነን ሥርዓት አራማጆች የመጨራሻ ዕድላቸው የቅርብ ማስረጃ ሆኗል::

ለአርባ ዓመታት ያህል ተዘጋጅቶ ኢትዮጵያን በመውረር ሕዝቧን ቅኝ አድርጎ ለመግዛትና ሀብቷንም ለመዝረፍ የመጣው የውጭ ጠላት ከሀገራችን ሊባረር የቻለው፣ በአርበኞች ትግል እንጅ በልመና ወይም በዓለም አቀፍ ሕግ አስገዳጅነት እንደልነበረ ሁሉ፣ የአምባገነን ሥርዓትም የሚወገደው በሕዝብ መራራ ትግል እንጅ፣ የሥርዓቱን አራማጅ ግለሰቦች በመለዋወጥ አይደለም:: የዘረኞቹ ቁንጮ ተወግዶ፣ በርሱ ምትክ ሌላ ጋሻ-ጃግሬ ቢተካ ሥርዓቱ ተለወጠ ማለት አይደለም:: አለቃን በጭፍራ መተካት፣ ደግሞ፣ ጉልቻን ከመለዋወጥ ያለፈ እርባና አያመጣም:: ወያኔዎቹ ፣ ታዲያ ፣ ይህንን እኮ ነው **“መተካካት”** እያሉ የሚያሾፉት !

የአምባገነን ሥርዓት አራማጆች በተለያዩ ምክንያቶች ከሥልጣናቸው ሊወገዱ ይችላሉ:: አንዱ

እድሜ ጠግቦ ሲሰናበት፣ ሌላው አገር ጥሎ ሲሸሽ፣ የቀረው ደግሞ በኅመም ምክንያት ይወገዳል:: የእነርሱ መወገድ፣ ሥር-ነቀል ለውጥ መጥቶ፣ ለተሻለ ሥርዓት በር በመክፈት ዴሞክራሲን የሚያጎናፅፍ አስተዳደርን ካላመጣ፣ የሕዝብ ተስፋ "ላም አለኝ በሰማይ ወተቷን የማላይ" ሆኖ ይቀራል:: በመሆኑም ሕዝቡ፣ ዕልመተ-ሕይወቱን እየገፋ ይቀጥላል:: ይህ ሂደት ግን ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ይሆናል:: የሕዝብ ቁጣና ምሬት ገንፍሎ ሲወጣ ግን፣ የሚያቆመው አንዳችም የምድር ኃይል እንደማይኖር ማስረጃ መጥቀስ አያስፈልገንም !

የማንኛውም ሀገር ሕዝብ፣ ሰብዓዊ ፍጡር በመሆኑ ብቻ፣ በተፈጥሮ ያገኘው መሠረታዊ ነፃነቱ የማይገሰስ፣ የማይደፈርና የማይነጠቅ እንጅ፣ ከማንም ኃይል የሚቸርም ሆነ የሚለመን አይደለም:: መጀመሪያ ልንጠቅህና በኋላ ስፈቅድልህ እየቆጠብኩ መብትህንና ነፃነትህን እለግስህላሁ የሚለው ባልት፣ ሊያታልል የሚችለው እራሱን አምባገነኑን እንጅ፣ ሕዝብን ሊሆን አይችልም:: በሃያ አንደኛው ክፍለ-ዘመን ለሚኖር ሕዝብ፣ በመካከለኛው ዘመን በነበረ አስተሳሰብ በሚዋዥቁ ጎጠኞች ሊታለልና ሊጭበረበር እንደማይችል በሀገራችን ያለው ሁኔታ በገሀድ ይመሰክራል:: የጎጠኞች ቁንጮ ከቦታው ተወገደ ማለት፣ ሥርዓቱ ተፈነገለ ማለት አይደለም:: ይህ ዘረኛና ጎጠኛ ሥርዓት ከሥረ-መሠረቱ ካልተወገደ በስተቀር ደግሞ፣ በኢትዮጵያ ሀገራችን የሕዝብ አመፅ እየተፋፋመና እየተስፋፋ ከመሄድ የሚያግደው ኃይል አይኖርም:: ሰላምና መረጋጋት የሚመጣው፣ የሃሰት ፕሮፓጋንዳን በቋሚነት እንዲሰራጭ በማድረግ አይደለም:: ይህን ሊካድ የማይቻል ሐቅ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር-እስከ ዳር በሚገባ ያውቀዋል:: በመሆኑም፣ የወያኔ ልብ-አድርቅ ፕሮፓጋንዳና የሥርዓቱ አቀንቃኞች መብተክተክ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ልብና አዕምሮ ሊማርክ ቀርቶ፣ ሲያልፍም አይነካው:: ይህ መታመን ካለበት፣ታዲያ ዛሬ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገውና የሚጠብቀው ለውጥ፣ የዘረኛው ሥርዓት ተወግዶ፣ ደሞክራሲያዊ አስተዳደርን የሚያጎናፅፈውን የሥርዓት ለውጥ ነው:: ለዚህ መተማመኛው፣ ሥር-ነቀል እንጅ የጥገና ለውጥ ሊሆን አይችልም:: ከዚህ ውጭ ማሰብም ሆነ መመኘት ደግሞ ከንቱ ድካም ይሆናል!

ከሃያ ዓመታት በላይ፣ በኢትጵያ ሕዝብ ላይ የተጫነውን ዘረኛ አምባገነን ሥርዓት በግምባር ቀድም ሲመራ የነበረ ግለሰብ በመሞቱ ምክንያት ፣ በኢትዮጵያ ለውጥ ሊመጣ ይችላል በማለት ራሳቸውን እየደለሉ ሌላውን ለማታለል የሚፍጨረጨሩትን ስንመለከት፣ ከመታዘብ አልፈን እናዝንላቸዋለን:: የሚታዘንላቸውም ፣ የሚያስቡትንና የሚሰሩትን አያውቁትም ከሚል ተላላነት ሳይሆን፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ እያታለልን ለመግዛት የሚያስችለን በር ተከፍቶልናል ብለው ላይና ታች መሯሯጣቸውን በመመልከታችን ብቻ ነው:: ከዚህም በቀር፣ አንድ መሠረታዊ የሆነ ሐቅን አለመረዳታቸው ፣ ዘወትር የሀገርን ፍቅርና የሕዝብን ከበሬታ ሊያገኙ አላስቻላቸውም::

በማንኛውም ሥርዓተ-መንግሥት ሥር ያለ ሕዝብ፣ ሊኖረው የሚችለው ዕድል፣ ከሁለት አማራጮች መካከል፣ እንደ ዕጣ-ፈንታው ሆነለት ተብሎ የሚመርጠው አንዱን ብቻ ይሆናል:: የመጀመሪያውና የተሻለው፣ በራሱ ፈቃድ፣ ስምምነትና ውሳኔ መሠረት የሚመሠርተው መንግሥት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ሳይወድና፣ ሳይስማማ፣ በጠብ-መንጃ አፈ-ሙዝ ተገዶ የሚጫንበት ነው:: ከነዚህ ሁለት አማራጮች የተለየ ለማስመሰል አምባገነኑን ሥርዓት ሕዝብን እያታለሉ ሌላ በማስመሰል ለመግዛት መሞከር ግን ብዙ ምዕራፍ የሚያስኬድ ዘዴ አይደለም:: ወያኔና ተባባሪዎቹ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ

በኃይልና በማታለል መግዛት እንችላለን ብለው ቢ.ያምኑም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን፣ በጠበንጃ ሰደፍ ተማምናችሁ ዕድሚያችሁን ማራዘም ትችሉ እንደሁ እንጅ ፣ ምንጊዜም ቢሆን እኛን ልታታልሉ አትችሉም የሚል መልስ ሰጥቷቸዋል።

ለአለፉት ሦስት ወራት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ምኅዳር እየተምታታና እየተዘበራረቀ የሚመታው አደንቋሪ  ነጋሪት፣ በወያኔ የሥልጣን “ መሽጋሽግ-መተካካት ” በሚሉት ዝባዝንኬ ላይ ያተኮረ እንደሆነ ይሰማል/ይታያል።  በመሠረቱ፣ በወያኔ ውስጥ የሥልጣን ሽግሽግም ይሁን፣ ብወዛ፣ የኃይል ሚዛን አሰላለፍም ይሁን ያመለካከት መሻሻል የሚባል ነገር ፈፅሞ የለም። አይኖርምም። ይህን ለማመን የሚፈልጉ ካሉ፣ “እየተገዙ መታገል” የሚል ዓርማ ያጠለቁ፣ በቀቢ.ፀ- ተስፋ ጉጉትና ምኞት ውስጥ ራሳቸውን እየደለሉ የሚኖሩ ክፍሎች ብቻ ናቸው። የየግል-ዕምነታቸው ሊከበርላቸው ቢችልም፣ ለሌላው ክፍል ግን “በዕርጎ ባኅር” ልትዋኝ የምትችልበት በር ተከፍቶልሃል የሚል ነጋሪት መጎሰም አይገባቸውም ነበር። የወያኔ የሥልጣን ማጠንከሪያውና መከላከያው፣ ማቆያውና፣ መራመጃው ንቅንቅና ፍንክች ሳይል፣ ገና ለገና መለስ ዜናዊ ተወግዷል በሚል ቁዘማ፣አዲስ የፖለቲካ ምዕራፍ ሊከፈት ይችላል እያሉ ማቋመጥ፣ ዝቅ ሲል፣ ራስን መደለል፣ ከፍ ሲል ደግሞ፣ አሁንም ቢሆን፣ የወያኔን ማንነትና ዓላማ በቅጡ ካለመረዳት የሚመጣ ተላላነት ነው። ወያኔዎቹ የሥልጣን “ሽግሽግ” እያደረግን ነው ቢሉ ፣ ያው የዘወትር ፕሮፓጋንዳ ስርጭት ተግባራቸው ስለሆነ ማንንም የሚያስገርም አይደለም። ምክንያቱም ፣ ለዕድሜ-ቀጥል ዓላማቸው የተወሰነ የፖለቲካ ኬሎ ሜትር ሊያስኬደን ይችላል ብለው ስለሚያምኑ ነው። የወያኔን ፍርፋሪ ለማግኘት የሚያቋምጠው ሌላው ክፍል፣ መለስ በመሞቱ ለውጥ ስለሚመጣ “እየተገዛን መታገላችንን” እንቀጥላለን በሚለው የተንበርካኪ አመለካከትና መለስ ስለሞተ፣ የሥልጣን “መሽጋሽግ” እያደረግን ስለሆነ የፖለቲካ ለውጥ ቀስ በቀስ ይመጣልና አርፈህ ተገዛ ! በሚለው መካከል ያለው ልዩነት የአባባል እንጅ በይዘት አንድ ነው። ሁለቱ የአንድ ሳንቲም ግልባጮች ናቸው። አንዱ ተንበርክኮ ለመገዛት ሌላው አንበርክኮ ለመግዛት የተደረገ የውል ስምምነት ነው። ከዚህ የሚያልፍ አይደለም። በብዥታ ዓለም ለሚዋልሉ ክፍሎች ግን በቀቢ.ፀ-ተስፋ ለመኖር ይረዳቸዋል!

<u>ዕውነታው ምንድን ነው</u>? የወያኔን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የፀጥታና የመከላከያ ተቋማት የመለስ ዜናዊ መሞት ሊለውጣቸው አይችልም። የወያኔ ሰዎች በሁኔታው የተርበተበቱና የተተራመሱ፣ የተደናገጡና የተወካቡ መሆናቸው ባይካድም፣ ድርጅታዊ መዋቅራቸውና የሠራዊታቸው ዕዝ ሰንሰለት ገና በሚገባ አልተናጋም። እስካሁን ሊያሰጋቸው የሚችል አንዳችም ተቀናቃኝ ቡድንም ይሁን ሌላ ስብስብ የለም። የውስጥ ፖሊሲያቸውም ይሁን የዲፕሎማቲክ ግንኙነታቸው ከያዙት ፍልስፍናም ይሁን ዓለማ ወይም የአሠራር ስልትና የጥፋት ጎዳና ሊያስቀይራቸው የሚችል ምክንያት የለውም። የጦር ኃይሉ፣ የፀጥታው ተቋማት፣ የስለላው መዋቅርና የመረብ ሰንሰለት፤ በመዳፋቸው ሥር እንዳለ ነው። የእያንዳንዱን የኅብረተሰብ ክፍል ኑሮ፣ እንቅስቃሴና ግንኙነት አምስት-በአምስት (5-በ5) የመዋቅር እይታ ሸብበው ይቆጣጠሩታል። በናዚ ጀርመን ጌስታፖ አምሳያና ሥልጠና የተዋቀረው የወያኔ የፌዴራል ፖሊስ፣ ተርቦ እንደተለቀቀ አውሬ ሰላማዊው ሕዝብ ላይ ለመጨከን ወደ ኋላ የሚልበት ርኅራሄ ልብ እንዳይኖረው ተደርጎ ሰልጥኗል። ጭካኔውና አረመኔነቱ፣ በደርግ ጊዜ ከነበረው ከነበልባል ጦር ቢበልጥ እንጅ አያንስም።

በወያኔ መንግሥታዊ መዋቅር ያሉትን ልዩ ልዩ አስተዳደር ዘርፎች፣ የዳኝነትና የፍትኅ ተገባራትን ሊፈፅሙ የተቋቋሙት መሥሪያ ቤቶች የሥርዓቱ የፖለቲካ መሣሪያ አገልጋዮች ሆነው ተዋቅረዋል:: ዳኞች፣ ጠበቆች፣ ህግ አስከባሪዎች፣ ሰላማዊ ፖሊሶች፣ ... የፍትኅ-ርትዕና የዳኝነት ጉዳይን ለማስከበርና የሕዝብን በደል ለማየትና ለመከላከል ሳይሆን፣ የዘረኛውን ሥርዓት ወንጀል ለመሸፈንና ለመከላከል ብቻ ተብለው የተዘጋጁ ናቸው:: አልፎ አልፎ ፍትኅን ባላቸው አቅም ለማስከበር የሞከሩ አንዳንድ ዳኞች የደረሰባቸውን የምናውቀው ነው:: የሃይማኖት ተቋማትና አባቶች ሳይቀሩ፣ በወያኔ የፖለቲካ ምኅዳር ቁጥጥር ሥር ውለዋል:: "**ይህ ዓለም ለምኔ፣ ለረፋድ ኅዳና ለግማሽ ቀን ዕድሜ**" ብለው መንነው፣ ገዳም ገብተው፣ በፆም-በፀሎት ተወስነው፤ ቅጠል በልተው፤ ዕፍኝ ጥሬ ቆርጥመው፤ ጥርኝ ዉሃ ተጎንጭተው፤ ለሀገር ሰላምና ለሕዝብ ብልፅግና ሌት-ተቀን የሚፀልዩትን መነኮሳትና መናንያን የሚኖሩባቸውን የዋልድባንና ሌሎች ገዳማትና ተቋማት ሳይቀር፣ እየደፈረና እያፈረሰ ይገኛል:: የሃይማኖት አባቶችንም እያሳደደና በሃይማኖት ተቋማት ላይ ጣልቃ-ገብነትን እያሰፈነ፣ መብታችን-ዕምነታችን ይከበር ያሉ ሙስሊም ዜጎችንም እያፈነ ያለ ሥርዓት፣ ከሥረ-መሠረቱ፣ መወገድ ያለበት እንጅ፣ በጥግንግን ለውጥ፣ ወይም አለቃውን በጭፍራው "በ**መተካካት**" አይደለም:: በኢትዮጵያውን እስላሞችና በሃይማኖታቸው ላይ የሚፈፀመው ግፍና በደል ዓለም የሚያውቀው ቢሆንም፣ የሥርዓቱ አራማጆች እስካልተለወጡ ድረስ የእስልምና ተከታይ ወገኖቻችን ስቃይና የሕሊና ሰቆቃ አያባራም:: የእነርሱም ትግል የትግላችን ዘርፍ በመሆኑ ተቃውሞው ይቀጥላል እንጅ፣ አይዘናጋም::

የኢትዮጵያ የትምህርት መስጫ ተቋማትም ሆኑ፣ መማሪያ መጻኅፍት ሳይቀሩ በጎሳ ላይ በተመሠረተ ሥርዓተ-ትምህርት የተዘጋጁና የተቃኙ በመሆናቸው፣ የወያኔን ዓላማና ፖሊሲ ለብዙ ጊዜ እንዲያገለግሉ ሆነው ተመስርተዋል:: ይህ የትምህርት ፖለሲ፣ የአሁኑንና መጭውን ትውልድ ገዳይ መሆኑ አይጠረጠርም:: **የነገዋ ኢትዮጵያ እንዳትኖር፣ የዛሬውን ትውልድ መግደል፣ የወያኔ ስትራተጅያዊ ወይም ዘላቂ ዓላማ በመሆኑ፣ የመለስ አልጋ-ወራሾች የርሱን ራዕይ እንከተላለን ማለታቸው አያስደንቅም**:: የመለስ "ራዕይ" <u>ሳይበረዝና ሳይከለስ</u>፣ ይቀጥላል:: ማለት፣ ለአለፉት 21 ዓመታት የተንሰራፋው፣ የአንድን ብሔረሰብ የበላይነት ለማስከበር የተመሰረተው ሥርዓት እንዳለ ይቀጥላል ማለታቸው ነው:: ይህም ማለት፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ መከራና ስቃይ፣ ረሀብና ችግር፣ እስራትና ስደት፣ ጥቃትና ውርደት ፣ ድኅነትና እርዛት በከፋ መልኩ ይቀጥላል ማለት እንደሆነ ግልፅ ነው:: ባዕዳን ኃይላትም የኢትዮጵያን ለም መሬትና ሀብት እንደልባቸው መበዝበዛቸውን ይቀጥላሉ ማለት ነው:: የሰብዓዊ-መብቶችና የዜጎች ክብር መጣስ እንደነበረ ይቀጥላል ማለት ነው:: የወያኔ እስር ቤቶችና ማጎሪያ ቤቶች በብዛት በመላ ሀገሪቱ መጥለቅለቃቸው እንደሚቀጥል ዕሙን ነው:: በመጨረሻም፣ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር፣ ዜጎቿም እንደ አንድ ሕዝብ ያለመቀጠላቸው ሂደት እየተፋጠነ ይሄዳል ማለት ነው:: ስለሆነም፣ የመለስን ሞት ተከትሎ የመጣው "<u>መተካካት</u>" ለፖለቲካ ቁማር ፍጆታና ለምዕራባውያኑ አለቆቻቸው የእጅ መንሻ ተብሎ የተደረገ የወያኔ መድረክ ተውኔት እንጅ፣ በዕርግጥ፣ ለኢትዮጵያ አዲስ የብሩኅ ተስፋ አድማስ የሚያሳይ ውጋገን አልከፈተም:: አይከፍትምም:: ለዚህም ነው ዛሬ፣ ኢትዮጵያ ሕዝብ፣ መሠረታዊ ለውጥ ካልመጣ የሀገራችን ሁለንተናዊ ችግሮች፣ "ሊፈቱ ቀርቶ ፣ ሊቀረፈቱ አይችሉም!" እያለ የሚጮኸው!

የኢኮኖሚ አውታሮችና የገንዘብ ተቋማት፣ የንግድና የገበያ ልውውጦችና መናኸሪያዎች የአስመጭና ላኪ ንግዶች፣ በሙሉ ከአንድ ብሔር በመጡ ግለሰቦች ሙሉ መዳፍ ስር ናቸው:: የማምረቻ ፣ ማከፋፈያና ማደያ ተግባራት እንደዚሁ በወያኔ ጥብቅ ቁጥጥር ስር እንደሆኑ ነው:: የመገናኛ ብዙኃን፣ ጋዜጦችና ማተሚያ ቤቶች፣ የኢንተርኔት/ድረገጽ ግንኙነቶች፣ ሌሎች የኢሌክትሪክ መገልገያዎችና ቴክኔሎጂ-ነክ፣ መሳሪያዎች ሁሉ ወደ ሕዝብ እጅ እንዳይደርሱ ጥብቅ ቁጥጥር ተደርጎባቸዋል:: ይህም የሚያሳየው፣ ይህ የገዥ መደብ ፣ ጠቅላላ ሀገሪቱን ሆነ፣ መላው ሕዝቧን፣ በሁለንተናዊ መልኩ፣ በፈላጭ ቆራጭነት ተቆጣጥሮ መግዛቱን የሚያረጋግጥ ሥርዓት እንደገና በአዲስ መልክ ተጠጋግኖ መቀጠሉ ዕሙን መሆኑን ብቻ ሳይሆን፣ ኢትዮጵያንና ዜጎቿን በአዲስ ጥርስ ለመጋጥ ወደተዘጋጀ ሁለተኛው ረድፍ በላዒ-ሰብ ሥርዓት መሸጋገሩን የሚያረጋግጥ ነው::

የአምባገነን ሥርዓት፣ የአገዛዝ ዕድሜዉን ለመቀጠል የሚወሰደው እርምጃ ሕዝቡን መከፋፈል ብቻ ሳይሆን፣ እያደኸየና እያደነቆረም ጭምር በመሆኑ ፣ ወያኔዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ ፣ የኢንተርኔት ነፃ ተጠቃሚና የቴክኔዎሎጂ ዕውቀትን በሙሉ ነፃነት እንዳያገኝ ማድረጋቸው፣ ማንንም የሚያስገርም አይደለም:: ባለፈው ዓመት በዓረብ-ፀደይ ሕዝባዊ አመፅ ሂደት፣ የኢንተርኔትና የኤሌክትሮኒክስ ግንኙነት፣ የአረብ ሀገር አምባገነኖችን ለማስወገድ የተጫወተውን ወሳኝ ሚና በሚገባ ስለተረዱ፣ "ነግ በኔ ይደርሳል" ብሎ በመርበትበት፣ የወያኔ ዘረኛ ቡድኖች ይህንን ቢያደርጉ አይፈረድባቸው:: ይህ የመከላከያ ዘዴ ግን የሕዝባዊ አመፅን ሂደት አይገታወም:: ቻይናዎችም በዚህ ረገድ አበክረው ቢረዷቸውም እስከመጨረሻው ድረስ አብረዋቸው እንደማይከርሙ ግልፅ ነው:: ከቻይና አፋኝ ሥርዓት ጋር በብዙ መልኩ የሚፈረጀው ይህ የአንድ ገዥ ፓርቲ አምባገነን ሥርዓት ሙሉ በሙሉ ካልተወገደ ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ የለውጥ ጭላንጭል ይመጣል ተብሎ የሚታሰብ አይደለም:: ይህ ሥርዓት ፣ በሥልጣን ለመቆየት የሚያስችለውን ማነኛውንም ትብብር የሚያደርግለት አገርም ይሁን ኩባንያ ካገኘ ግን፣ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም አሳልፎ ከመስጠት ወደኋላ እንደማይል በተግባር አረጋግጧል::

በሀገራችን የዲፕሎማቲክ ታሪክ፣ የውጭ ኃይላት፣ በተለይም ምዕራባውያኑ፣ የኢትዮጵያን ውስጠ-ምሥጢር እንደዛሬ ተከፋፍቶ አልተሰጣቸውም:: የእነርሱን ጥቅም በትጋት ማስጠበቁ ብቻ ሳይሆን፣ ሲጠሩት አቤት ሲልኩት ወዴት የሚል እንደ ወያኔ ዓይነት ተላላኪ አግኝተው ስለማያውቁ፣ ጥቅማቸው እስከተጠበቀ ድረስ፣ የመለስ መሞት-አለመሞት ደንታ አይሰጣቸውም:: በታማኝነት መልምለው ያሰለጠኗቸው ሌሎች ወያኔዎች ስለአሏቸው፣ በወር ተራ ሊያገለግል የሚችለውንና በታማኝነቱ የማይጠረጥሩትን አንዱን ተጠባባቂ ታማኝ አገልጋይ መርጠው በቦታው ማስቀመጥ አልተሳናቸውም::

የውጭ ኃይላት፣ በኢትዮጵያ ያገኙት ጥቅማቸው ስጋት ላይ እስካልወደቀ ድረስ፣ ስለ ሀገራችን የሰብዓዊ መብቶች መጣስ፣ ስለ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር፣ ስለ ሕዝብ ኑሮ ማሻሻልም ሆነ፣ ስለ ብሔራዊ ጥቅማችን ያስቡልናል ብሎ ማለት አይቻልም:: ይህ የምዕራባውያኑ አመለካከትና አፈፃፀም በሌሎቹም ሦስተኛ ዓለም በሚባሉት ሀገራት የሚያከናውኑት ስለሆነ፣ ለእኛ ኢትዮጵያውያን የሚያስገርም አይደለም:: በታሪክ ምፀትነቱ የሚያስደንቀን ግን፣ በሽህ

የሚቆጠሩትን ጀግና ኢትዮጵያውያንን ያፈራች፣ ይህች የትግራይ መሬት ፣ እነዚህን ከሃድያንም መውለዷ ነው፡፡ እነሱን የመሰሉ ከሌላውም የኢትዮጵያ አካባቢ አልበቀሉም፤ የሉም ማለት አይደለም፡፡ ታዲያ እንደነዚህ ካሉ ከሀዲዎች፣ ለሀገር የሚጠቅም ምን ለውጥ ይመጣል ተብሎ ይጠበቃል?

የተመሠረቱበትን፣ የተደራጁበትንና የታገሉበትን መሠረታዊ ዓላማ አንግበው፣ ምኒልክ ግቢ በመግባት ሥልጣናቸውን አደላድለው ኢትዮጵያን የማፈራረስ ዕቅዳቸውን ያላንዳች ስጋትና ጭንቀት በመፈፀም ላይ የሚገኙት፣ እነኝህ የዘረኛ ሥርዓት አራማጅ ቡድን አባላት፣ የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ጥፋት የመጨረሻ ምዕራፍ ሳይዘጉ ዕንቅልፍ ይወስዳቸዋል ተብሎ አይጠበቅም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን "አጥፊዎቿ ይጠፏታል እንጅ፣ ሀገራችንስ አትጠፋም" ብሎ በፅናት እየታገለ ቢገኝም፣ "መተኪያው ምንድን ነው? የወደፊቱስ የኢትዮጵያ የፖለቲካ መልከዓ-ምድር ምን ይመስላል? የተጠናከረ ተቃዋሚ ኃይልስ እንዴት ይፈጠራል? ለመሆኑ የሀገራችን ችግሮች መፍትሂያቸው ምንድን ነው?" እና የመሳሰሉትን መሠረታዊና አሳሳቢ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ላይ ይገኛል፡፡ ኢሕአፓም፣ እንደ ኢትዮጵያዊነቱ፣ እነኝህን የኢትዮጵያ ሕዝብ መሠረታዊና አንገብጋቢ ጥያቄዎች አብሮ ይጠይቃል፡፡ ጥያቄው ግን፣ የተነሱበትን የትግል ዓላማ፣ ሕዝባዊ አደራና፣ የገቡትንም ቃል-ኪዳን በፅናት ጠብቆ መታገል? ወይስ ምንም መሠረታዊ ለውጥን በማያመላክት ወቅታዊ የፖለቲካ መለዋወጥ ብዥታ ውስጥ ገብቶ ፣ ዓላማን ስቶ፣ በጥቅመኝነት ራስን ማዋረድ? የሚለው ዐቢይ ጉዳይ ነው፡፡ ለእነኝህ ጥያቄዎች፣ ፓርቲው ያለ ከንቱ ውዳሴ፣ በልበ-ሙሉነት አወንታዊ መልስ መስጠት ይችላል፡፡ ይህንንም ሐቅ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብም ያረጋግጥለታል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ፣ እንደ እንቆቅ እየጎመዘዘውም ቢሆን፣ ወያኔ ያደረሰበትን፣ ብሔራዊ ውርደት፣ ሀገራዊ ጥቃት፣ መከራና ችግር እንዲሁም፣ የግል ነፃነት ማጣት ተገድዶ የተጫነበት መሆኑን በቁጭት ይገነዘባል፡፡ ይኽ ሁሉ ጥቃትና ብሔራዊ ውርደት የደረሰበት ግን፣ የውስጥና የውጭ ባላንጣዎች ስለተባበሩበት እንጅ፣ ከአንድ የኢትዮጵያ ክፍል በመጡ ዘረኛ ቡድን አባላት ዕውቀትና ችሎታ ብቻ እንዳልሆነ አሳምሮ ይረዳዋል፡፡ ቢሆንም፣ በሀገሩ ላይ የደረሰውን ችግር ተባብሮ ላለማስወገድ ግን ፣ እንደ ቋሚ ምክንያት ሆኖ እንደማቆጥር ይረዳል፡፡

"ቤታቸውን ከፍተው ሌባን ያማርራሉ !" የሚለው ይትበኃል አስተናጋጅ አለው ብሎ ለማመን ቢያስቸግርም፣ በሀገሩ ላይ ችግር ያመጡበትን ባላንጣዎቹን ላለማውረድ ግን ማጠየቂያ ሊሆን አይችልም፡፡ በአንድ ሀገር ላይ የደረሰውን ብሔራዊ ችግር ለማስወገድ፣ የመላው ዜጋ አንድነትና ትብብር ወሳኝ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ዜጎች የየራሳቸውን የግል ነፃነትም ይሁን ሰብዕና ፣ የሀገራቸውንም ብሔራዊ ክብርና ታሪክ እራሳቸው ካላስከበሩ ማንም መጥቶ ነፃ እንደማያደርጋቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ መንገር ድፍረት ብቻ ሳይሆን ድንቁርናም ጭምር ይመስለናል፡፡ ምክንያቱም ለዘመናት የሀገሩን ነፃነትና ኀልውና እንዲሁም ልዕልና ሲያስከብር የኖረ ሕዝብ በመሆኑ ነው፡፡

ይህ የዛሬው ትውልድ ግን ሀገሩ እይተቆራረሰች፣ ድንበሯ እየተሸራረፈ፣ ሃይማኖት፣ ታሪክና ዕምነት መበረዝ በቻ ሳይሆን ቀስ በቅስ እየጠፋ መሆኑን ሳይወድ በግድ እንዲያይ እተየደረገ ነው፡፡ ይህን የሚያስፈፅሙ ግለሰቦች በሥልጣን ኮረቻ ላይ እያሉ፣ የሀገሪቱ ሁኔታ ወደ መልካም የለውጥ አቅጣጫ እያመራ ነው ብሎ ማለት፣ ኃላፊነት የጎደለው አባባል ብቻ ሳይሆን ጥቅመኝነትም ጭምር ነው፡፡

በሀዘን በሚኮማተረው የኢትዮጵያ ሕዝብ በኩል እንደእኩይና ምፀት ይቆጠራል። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተባብሮ ለለውጥ ትግል እንዳይነሳና እንደይተባበር ሆን ተብሎ የሚከናወን ትጥቅ-አስፈች የመሰሪዎች ከንቱ ተንኮል ነው። ይህን ዝናር-አስፈች ውኅርንብር ሁሉም ዜጋ ነቅቶ ካልተቋቋመው፣ ጥቃቱና ቁጭቱ ተጠናክሮ ይቀጥልበታል። አንድነትን አጠንክሮ መተባበር የጥቃትና የውርደት ማስወገጃ ኃይል እንደሆነ፣ የኢትዮጵያን ጥፋት የማይመኘው ዜጋ ሁሉ እንደሚያምንበት አንጠራጠርም።

በበኩላችን፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የደሰረውን ጥቃት፣ ውርደት፣ ግፍ፣ አንገት-መድፋት፣ ቁጭትና ብስጭት፣ በየቤቱ መብተክተክና መብሰልሰል በአርምሞ ብቻ አናልፈውም። እኛም በወገናችን ላይ የተፈፀመበት በደል ሁሉ ተካፋዮች ነን።  ይህም የአጥንቱ ፍላጭ፣ የሥጋው ቁራሽ፣ የደሙ ፍሳሽ፣ አንድ አካል-አንድ አምሳል በመሆናችን ብቻ እንጅ፣ ሌላ ዓብነት ኖሮን አይደለም። ከወያኔና መሰሎቹ ጋር ያለን መሠረታዊ  ልዩነትም ይኸው ነው። በእኛ በኩል ፣ የኢትዮጵያ ሁለንተናዊነት ፣ የመላው ሕዝቧ አንድነትና ዕኩልነት ፣ የሀገር ሉዓላዊነትና የግዛት ልዕልና እንዲሁም ብሔራዊ ነፃነት ለድርድር የሚቀርብ አይደለም። ያማ ባይሆን ኖሮ፣ ከባዕዳን ኃይላት ጋርም ይሁን ከሌሎች አገር-አፍራሽ ቡድኖች ጋር በመመሳጠር፣ ወደ ምኒልክ ግቢ የሚያስገባውን በር መክፈት ይቻል ነበር። ለውጭ ኃይላት ተፅዕኖ ባለመንበርከካችንና ከሀገር አፍራሽ ቡድኖች ጋር ባለመመሳጠራችን የዓላማ ፅናት አቸናፊዎች እንጅ፣ ተንበርካኪዎች ባለመሆናችን፣ ምን ጊዜም ከድል አድራጊነት ማማችን አንወርድም። በመሆኑም፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ሥር-ነቀል ለውጥ መጥቶ ሀገራችን ከወያኔ ዘረኛ አገዛዝ ነፃ እስከምትወጣ ድረስ ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን በመቆም ትግላችንን እንቀጥላለን !

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !
ኢትዮጵያ በነፃነቷ ለዘለዓለም ትኖራለች !
እናቸንፋለን !!